# መቅድም

ምርምርና ሥርጸት ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዐዲስ ሥራ አይደለም፡፡ ቤተ ክርስቲያኒቱ ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ በራሷ መንገድ እና አውድ ጥናት ታካሂዳለች፡፡ ቤተ ክርስቲያኒቱ በብራና ባህሏ አማካኝነት ለብዙ መቶ ዓመታት ዕውቀትን እያሰራጨች ትገኛለች፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ የኅትመት ዓይነቶችና ዘዴዎች እየተሻሻሉ እና እየተለወጡ መጥተዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያኒቱም በዘመናዊው ዘዴ ዕውቀትን የሚያመርቱ እና የሚያሰራጩ ተቋማትን አቋቁማለች፡፡ ከእንዲህ ዓይነት ተቋማት አንዱ ከ30 ዓመታት በፊት የተቋቋመው ማኅበረ ቅዱሳን ነው፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን በስሩት የሚሰራጩትን የሐመር መጽሔትን እና ስምዓ ጽድቅ ጋዜጣን ሲያሳትም ቆይቷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የማኅበረ ቅዱሳን የጥናትና ምርምር ማእከል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ዘመናዊ የምርምር ኅትመቶች መድረክ ኾኖ እንዲያገለግል ከዐሥር ዓመታት በፊት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥናት መጽሔትን አቋቁሟል፡፡ ይህ ሰባተኛው የኢ.ቤ.ጥ.መ. ቅጽ ኅትመቱ ለአራት ዓመታት ከተቋረጠ በኋላ የወጣ ነው፡፡ የኢ.ቤ.ጥ.መ. አርትኦት ቦርድ ለተፈጠረው መቆራረጥ ይቅርታ እየጠየቀ የዚህ ቅጽ ኅትመት እውን እንዲኾን አስተዋጽዖ ላደረጉ ጸሐፍ አቅራቢዎች እና ገምጋሚዎች ምስጋናውን ያቀርባል፡፡

የአሁኑ የኢ.ቤ.ጥ.መ. እትም በዋናው ጽሑፍ ውስጥ የተጠቀሱ ተዛማጅ ጽሑፎችን ለመጥቀስም ኾነ ዋቢ መጻሕፍትን ለማቅረብ የአሜሪካ ሥነ ባሕርይ ማኅበር (APA) 7ኛ እትም) ቅርጽን ተከትሏል፡፡ የኅትመት ቋንቋዎቹም ዐምስት፡ ማለትም ግእዝ፣ አማርኛ፣ አፋን ኦሮሞ፣ ትግርኛ እና እንግሊዘኛ እንዲኾኑ በግልጽ አስቀምጧል፡፡

በዚህ ቅጽ ስድስት መጣጥፎች ቀርበዋል፡፡ አራቱ በአማርኛ ሲጻፉ ሁለቱ በእንግሊዘኛ የተጻፉ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው መጣጥፍ የግእዝ ፊደል ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች መጻፊያነት መዋል እንደሚችል የመከራከሪያ ነጥቦችን ያቀርባል፡፡ ሁለተኛው ጽሑፍ ድጓ በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ምእመናን ማኅበራዊ ሕይወት የሚጫወታቸውን ልዩ ልዩ ሚናዎች ያቀርባል፡፡ ሦስተኛው መጣጥፍ ስለ ታዋቂው የአንድምታ ትርጓሜ መምህርና የትርጓሜ ትምህርት ቤት መሥራች መምህር ኤስድሮስ ታሪክና የመሠረቱትን የአንድምታ ትምህርት ቤት በዝርዝር ያቀርባል፡፡ አራተኛው መጣጥፍ ስለ የበቆጂ ጨፋ መካነ ሕይወት መድኃኔ ዓለም ደብረ ቁስቋም አንድነት ገዳም መገደም መነሻ ትርክቶች ዝርዝር ጉዳዮችን ያቀርባል፡፡ ዐምስተኛው መጣጥፍ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዐውድ ውስጥ ቁሳዊ ያልኾኑ ንብረቶችን ለመገመት የሚረዱ ዘዴዎችን ይዳስሳል፡፡ የመጨረሻው መጣጥፍ በኢትዮጵያ ያለውን ታሪካዊ የመንግሥት እና የሃይማኖት መስተጋብር ይገመግማል፡፡

# Preface

Research and dissemination is not a new undertaking to the Ethiopian Orthodox *Tewahedo* Church. The church has been conducting research in its own terms since its establishment. The Church has been disseminating knowledge through its well-established parchment (*branna*) culture for hundreds of years. Through time the publication types and means have evolved. The church has established institutions that produce knowledge and disseminate through modern methods. Once such centers is *Mahibere Kidusan* , established more than 30 years ago. *Mahibere Kidusan* has been publishing the widely distributed *Hamär* magazine and *Səmə'a S'ədq* newspaper.

The Research Center of *Mahibere Kidusan* established the Journal of Ethiopian Church Studies more than a decade ago to serve as a forum for modern research publications focused on issues related to the Ethiopian Orthodox Church. This seventh volume of JCES comes after the publication was interrupted for four years. The editorial board of JCES apologizes for the interruptions and extends its gratitude for those contributors and reviewers who made the publication of the current issue a reality.

The current issue of JECS has introduced APA (7$^{th}$ edn.) style for both intext citations and references. The journal now has specified the languages of the publication to be five: Ge'ez, Amharic, Afaan Oromoo, Tigrinya and English.

There are six articles in the current issue. Four of them are written in Amharic while two of them are written in English. The first article presents the an argument for the adoption of the Ethiopic Script or *fidäl* for Ethiopian languages. The second article presents the different social roles that d*əggʷa* plays among the EOTC laity. The third article is about the well-known commentary school founder Esdros. The fourth article is about the historical background of the establishment of the *Bäqqoǰi Č'äffa Mädhane 'Aläm Däbrä̈Qusqʷam* Unity Monastery. The fifth article presents a review of methods used to value nonmaterial assets in the context of the Ethiopian Orthodox *Täwahədo* Church. The final article reviews the historical state-religion interactions in Ethiopia.